ግልፅ ደብዳቤ፤

የሴቶችን በፋይናንስ ውስጥ የመካተት ኃይልን ተግባራዊ በማድረግ የዲጂታል ፋይናንስ አቅም ወሳኝ ነው፤ ሆኖም ሁላችንም የድርሻችንን መወጣት ይኖርብናል፡፡

አንዲት ሴት በፋይናንስ ውስጥ ስትካተት በራሷ ስም ያሉ ኃላፊነት ያለባቸው የፋይናንስና የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ይኖሯታል፣ ፍላጎቶቿን በሚያሟላ መልኩ የፋይናንስ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ትሆናለች፣ የመቋቋም ችሎታን ለመገንባትና ሥራዋን ለማሳደግ ዕድሎች ይኖሯታል፡፡ በሥራዋ በምትካሂዳቸው ቅጥሮች ጥቅሞቹን ወደህበረተሰቡ ታስተላልፋለች፣ ልጆቿም በትምህርት ገበታ ይቆያሉ፣ የወደፊት የኤኮኖሚ ችግሮችን ለመቋቋም ገንዘብ ትቆጥባለች፡፡

ሴቶች በመረጃ ላይ የተደገፉ ምርጫዎችን እንዲያደርጉና የዲጂታል መሳሪያዎችን በውጤታማነት እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸውና በዲጂታል ፋይናንስ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ የሚኖራቸውን እምነት የሚገነባ ዕውቀት የሚሰጣቸው የፋይናንስ አካታችነት ዋነኛው አስቻይ የዲጂታል ፋይናንስ አቅምን መገንባት ነው፡፡ የተሻሻለ የዲጂታል ፋይናንስ አቅም የፋይናስ አገልግሎቶችን በአስተማማኝነትና በውጤታማነት ለመጠቀም ያነሳሳል፣ ያስችላልም፡፡

የአካባቢ፣ የቀጠናና የዓለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት በሴቶች ዲጂታል ፋይናንስ አካትችነት ሂደት በማፋጠን የጋራ ዓላማ ሥር እንደሚያሰባስብ አካል የሴቶች ዲጂታል ፋይናንስ አካታችነት ተሚጋች ማዕከል ሴቶች የፋይናንስ ግቦቻቸውን ለማሳካት ኃላፊነት ያለባቸው ዲጆታል የፋይናንስ አገልግሎቶችን በውጤታማነት የመጠቀም ችሎታቸው ሴቶች ኤኮኖሚያዊ ኃይል እንዲኖራቸው በሚደረገው ጉዞ መረማመጃ ነው፡፡

ሴቶች የኤኮኖሚ ኃይል እንዲኖራቸው ከማስቻል ባለፈ የዲጂታል ፋይናንስ አቅም የተሻሻለ የደንበኛ ተሳትፎ ያበረታታል፣ በመደበኛ የፋይናንስ ዘርፍ ላይ ያለውን እምነትም ያጎለብታል፡፡ ከሂሳብ እንቅስቃሴ መፍትሄዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶች ውስጥ የዲጂታል ፋይናንስ አቅም ሲቀናጅ ደንበኞች ይበልጡኑ በአገልግሎቶቹ ይሳተፋሉ፡፡ በባንግላዴሽ DBBL መፍትሄው ራሳቸውን ችለው በገንዘብ ዝውውር የሚጠቀሙ ደንበኞችን ቁጥር በ 76% አሳድጎታል፡፡ በኢንዶኔዥያ BRI መፍትሄውን በተቀበሉ ተጠቃሚዎች አማካይ ተቀማጭ በ17 እጥፍ አድጓል፡፡ ይህ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎችን የፋይናንስ ጥቅም ውሎ አደር ያሳድገዋል፣ ቁጥራቸው የበዛና ዘርፈ ብዙ ደንበኞችን ያገለግላል አዳዲስ ዕድሎችን ይፈጥራል፣ መንግሥታትና የሲቪል ማህበረብ ድርጅቶችም የፋይናንስ አካትችነት ግቦቻቸውን እንዲያሳኩ ያስችላቸዋል፡፡

የሴቶች ዲጂታል ፋይናንስ አካትችነት ተሚጋች ማዕከል በሰፊ የግንኙነት መረቦቻችን የሴቶችን ዲጂታል ፋይናንስ አቅም ለመደገፍ ቁርጠኞች ነን--ሆኖም ይህንን ሥራ ብቻችንን ልንሠራው አንችልም፡፡ ለዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን ይበልጥ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት የመንግሥታትን፣ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎችንና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የጋራ እገዛ እንፈልጋለን፡፡

ዛሬ የሴቶች ዲጂታል ፋይናንስ አካታችነት ተሚጋች ማዕከል እነኚህን ሦስት ቡድኖች ተከታዮቹን አሰፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስኖና በዓለማችን ደቡባዊ ክፍል ያሉ ሴቶችን የዲጂታል ፋይናንስ አቅም ግንባታን እንዲያበረታቱ ጥሪያችንን እናስታላልፋለን፡፡

መንግሥታት

1. የዲጂታል ፋይናንስ አቅምን ከብሄራዊ ዲጂታል ፋይናንስ አካታችነት ጥረቶች ጋር ማስተሳሰር፤ የፋይናንስ አካታችነትንና የኤኮኖሚ አቅም ደረጃን ለማሻሻል መንግሥታት ወሳኝ ዲጂታል መሠረተ ልማት ጥረቶችን ከመስተጋብር የክፍያ ስርአቶች፣ የዲጂታል መለያ ስርአትና የዳታ አስተዳደር ከዲጂታል ፋይናንስ አቅም የድጋፍ ፕሮግራሞች ጋር በጋራ ማካሄድ፡፡ ይህ ሴቶች በዲጂታል ክፍያ ስረርአት ያላቸውን እምነትና አጠቃቀማቸውንም...ያጎለብታል፡፡ መንግሥታዊ አካላት በብሄራዊ የፋይናንስ አካታችነትና ዲጂታል ስትራቴጂዎችን ትግበራ የዲጂታል ፋይናንስ አቅምን በማህበራዊ ጥበቃና ሌሎች ከአጠቃቀም ጋር የተሳሰሩ ትምህርታዊ ተግባራት ውስጥ ማካተቱ ቅደሚያ ሊሰጡ ይገባል፡፡

2. ከባለድርሻ አካለት ጋር አጋርነት መፍጠርና ወሳኝ የሆኑ ደንበኞች ይበልጡኑ የዲጂታል ፋይናንስ አቅም ችሎታዎች የሚስፈልጓቸውን የቃላት አረባብ ነጥቦች ለመረዳት ከሴቶች ጋር መመካከር፤ መንግሥታት በክፍል ውስጥ የተመሰረቱ አጠቃላይ የፋይናንስ ግንዛቤ ስልጠናዎች ወጪ የሚሆኑ ግብአቶችን ለባለድርሻ አካላት (የሴቶች መብቶች ድርጅቶች፣ የሸማቾች ማህበራትና የአካል ጉዳተኞች ማህበራት የመሳሰሉት) ጋር በጋራ ወደመሥራት አዞሮ የተለዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ከመጠቀም ፍላጎት ጋር እንዲገጣጠሙ በሚያስችል መንገድ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶች ማቅረብ፡፡

3. ተገቢ የ FSP ተጠያቂነት ስርአቶችን መተግበር፤ ይህ ከ FSPs ጋር በመመካከር የዲጂታል ፋይናንስ አቅምን እንደ ምርት እድገትና አቅርቦት ለማካተት የኢንዱስትሪውን ተጠባቂ ውጤቶችና መመሪያዎችን ያካትታል፤ የዲጂታል ፋይናንስ አቅምን ዋጋ ያላቸው ሃሳቦች ለማራመድና ችሎታቸውን ሳያከትት ለሁሉም ደንበኞች የደንበኖች ጥበቃ ለማድረግ መንግሥታት እነኚህ መመሪያዎች መተግበራቸውን ክትትል ማድረግና በዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶች ተደራሽነትና አጠቃቀምን እኩልነትን ለማሰፈን ያለሙ ተግባራት በጾታ የተለየ ዳታ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

የፋይናንስ አገልግሎቶች አቅራቢዎች

1. የዲጂታል ፋይናንስ አቅም ንድፍ፡ FSPs ንድፋቸውን በኃላፊነት መንፈስ እንዲያወጡና የሴቶች ደንበኞችን ግንዛቤ፣ በራስ መተማመንና ችሎታዎቻቸውን ለማጎልበት የፋይናንስ አቅም ግንባታን በዲጂታል ፋይናንስ መፍትሄዎቻቸው ውስጥ እንዲያቀናጁ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡ እንዲህ አይነት የተቀናጁ አቀራረቦች የደንበኞችን ግቦች ለማሳካት የምርቶችን አጠቃቀም በማበረታታት ከተለመደው የፋይናንስ ግንዛቤ አቀራረቦች አልፈው ይሄዳሉ፡፡ የዲጂታል ፋይናንስ አቅም ሲቀናጅ የገንዘብ ልውውጥ መጠንና ድግምግሞሽ እንደሚያድግና የተጨማሪ ምርቶችና አገልግሎቶች ተሽጋሪ ሽያጭ እንደሚያድግ አይተናል፡፡
2. ጾታን ያማከሉ የተሳትፎ ዕድሎች ማቅረብ፤ በደንበኞች የማመር ፍላጎቶች ስፋት የተነሳ FSPs ከተለያዩ ክፍሎች የሚመጡ ሴቶችን ለማስተናገድ የዲጂታል ፋይናንስ አቅም መልእክቶችን ውስጣዊ ለማድረግ ያሉ መሰናክሎችን ቀንሰው ወደተግባር እንዲለወጡ ሊረዱ የሚችሉ በተለምዶ ይብልጡ አስተማማኝ የሆኑ የግንኙነት መረቦችን ጨምሮ የተለያዩ የስርጭት

ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፡፡ በተጨማሪ FSPs አንደ ችሎታ፣ ዘር፣ ሃይማኖትና ፍለሰትን የመሳሰሉ ከጾታ ጋር የሚገናኙ ነጥቦችን ከግንዛቤ ማስገባት አለባቸው፡፡ የተለያዩ ደንበኞች የሚማሩት በተለያዩ መንገዶች ነው፡፡

3. በጾታ የተለዩ መረጃዎችን በመጠቀም ግቦችን ማስቀመጥና እርምጃዎችን መከታተል፤ በገበያ አውድ ጠንካራ የፋይናንስ ግንዛቤ ግቦች፣ ጠንካራ ክትትል፣ ግምገማና መማማር ለብሄራዊና የኢንዱስትሪ ደረጃ ግቦች አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡ እርምጃ ማለት የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶች ተግባራዊ አጠቃቀምን እንዲሁም ደንበኞች ጥበቃ እንዲደረግላቸው ማረጋገጥን ማካተት አለበት፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

1. ለሴቶች የዲጂታል ፋይናንስ አቅም ስልጠና መስጠትን ቅድሚያ መስጠት፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከFSPs እና ከወንዶች ጋር በመተባበር የዲጂታል ፋይናንስ አቅም በሴቶች ሕይወት ስለሚፈጥረው ከፍተኛ ዋጋ ግንዛቤ ለማስጨበጥ አስተማማኝ የማህበረሰብና የአቻ ትስስሮችን እንዲጠቀሙ ጥሪ እናቀርባለን፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝም ሴቶችን FSPs እና መንግሥታትን ተጠያቂ የማድረግ መብታቸውን ሊያስተምሯቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ይዘትን ማደረስን ከፍ ለማድረግ  ሴቶች ሊሳተፉባቸው የሚችሉ ዲጂታል መገናኛዎችን መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ የስልጠናዎቹ ይዘትና አቅርቦት ተደራሽ መሆናቸውንና ሴቶቹ ባሉባቸው ቦታዎች እንደሚያገኟቸው ለማረጋገጥ ልዩ ትኩረት መሰጠት ይኖርበታል፡፡
2. የደንበኞችን ድምፆችና አመለካከቶች ከፍ ማድረግ፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የደንበኛውን ደምፅ ለማሰማትና የሴቶችን የዲጂታል የፋይንስ ተግዳሮቶች ለማሳወቅ ከመንግሥትና ከግሉ ዘርፍ ጋር አጋርነት መፍጠር አለባቸው፡፡ በተጨማሪም መንግሥታትና የፋይናንስ አገልግሎቶች አቅራቢዎች ሴቶች ዘንድ ደርሰው የዲጂታል ፋይናንስ አቅምን ለመገንባት እንደ ጠቃሚ አገናኞች ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡
3. በማህበረሰብ ውስጥ ተምሳሌቶች  የሚሆኑ ከተለያዩ ክፍሎች የተገኙ ሴቶችን መለየት እና/ወይም ማደራጀት፤ እነኚህ ተምሳሌቶች እምነትን ለማዳበር፣ ተሳትፎን ለማበረታተት፣ እንዲሁም መደበኛ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለመጠቀም ተጨባጭ ጉዳዮችን ያጎላሉ፡፡ በእነኚህ ተምሳሌቶች በኩል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከተለያዩ ማህረሰቦች በተውጣጡና የተለያዩ ችሎታዎች ባሏቸው ሴቶች ስም ግንዛቤዎችን ለማጎልበትና ለተደራሽነትና ለአካታቻነት ይሟገታሉ፡፡ በጋራ በመሥራት ለዲጂታል የፋይናንስ አቅም መንገዱን ልንጠርግ እንችላለን፡፡ ሴቶች የዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ ቤተሰቦችንና ሙሉ ማህበረሰቦችን ከፍ ያደርጋል፡፡ የዲጂታል ፋይናንስና የዲጂታል ክፍያ ስርአቶችን እንደ ወደፊት ስርአቶች የሚቀበለው የዓለም ክፍል እያደገ ሲሄድ ሴቶች ወደኋላ እንዳይቀሩ በማረጋገጥ በሚፈጥሯቸው ዕድሎች እምነትን መገነባት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡